# ጤናን ይምረጡ ፤ ቆዳ የሚያቀላን ያስወግዱ

## ቆዳዎን ይውደዱ

አንዳንድ ቆዳን የሚያበሩ ምርቶች በውስጣቸው **ሜርኩሪ** አላቸው እና ጤናማ አይደሉም። **መርዛማ** ናቸው። ሜርኩሪን ማየት ፤ በስሜት ማወቅ፣ ማሽተት ወይም መቅመስ አይቻልም ፤ እና ብዙውን ጊዜ የቆዳ ምርት ንጥረ ነገር ዝርዝር የተሟላ አይደለም።



### የጤና ምክሮች

- በቆዳ ምርትዎ ውስጥ ምን እንዳለ ይወቁ
- ቆዳዎን ደህንነቱ በተጠበቀ የፀሐይ መከላከያ ይከላከሉ
- ቆዳዎ እርጥበት እንዲኖረው እና ዉሀ አዘል እንዲሆን ያድርጉ

## ይከላከሉ

### ልጅዎን



ጡት በማጥባት ጊዜ፣ ልጅዎ በቆዳዎ ላይ ያለውን ማንኛውንም ነገር ወደ ውስጡ ይወስዳል።

### ራስዎን



ከቆዳ ምርቶች የሚገኘው ሜርኩሪ በቆዳዎ በኩል ይመጠጣል።

### ቤትዎን



እነዚህን ምርቶች መጠቀም እርስዎ እና ቤተሰብዎ በሚተነፍሱበት አየር ውስጥ ሜርኩሪ ያስገባሉ።

# ብዙ ቆዳ የሚያቀሉ ምርቶች ሜርኩሪ አሉዋቸው። አይግዙ ወይም አይጠቀሙ።

ይህ የተሟላ ዝርዝር አይደለም። በሚኔሶታ ውስጥ የተመረመሩ ብዙ ምርቶች ሜርኩሪ እና / ወይም ሌሎች ኬሚካሎች ነበሯቸው።
ለተጨማሪ ምሳሌዎች ይጎብኙ health.state.mn.us/topics/skin




## መጠቀሙን አሁን ያቁሙ



ሜርኩሪ ያለበት ምርት እየተጠቀሙ ከሆነ፣ አሁን መጠቀሙን ያቁሙ። ሰውነትዎ በተፈጥሮው ከጊዜ በኋላ ሜርኩሪውን ያስወግዳል።



ሜርኩሪ በህፃናት እና በልጆች በትምህርት ቤት የማስታወስ፣ አስተሳሰብ፣ ትኩረት እና ስኬት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል።



የቆዳ የማለስለሻ ምርቶችን የሚጠቀሙ ሰዎች የኩላሊት ወይም የነርቭ ሥርዓት ችግሮች ሊኖራቸውና ህመም እና ሽፍታ ሊያዳብሩ ይችላሉ።

## የት እንደሚጣል ይወቁ



ጎጂ የቆዳ ምርቶችን በቆሻሻ መጣያ ውስጥ አይጣሉ። ወደ አካባቢው ከገባ ሌሎችን ሊጎዳ ይችላል። የቆዳ ምርቱን ወደ የቤት አደገኛ ቆሻሻ ጣቢያ ይውሰዱ። በአካባቢዎ የአደገኛ ቆሻሻ ጣቢያዎችን በ pca.state.mn.us ያግኙ።


DEPARTMENT OF HEALTH
625 Robert St. North
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975


*ይህንን መረጃ በተለየ ይዘታና አቀራረብ ለማግኘት፣ ይደውሉ 651-201-4899.* REV 05/2018